የሰበር መ/ቁ. 19258

ሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

አቶ ብርሃኑ አመነው

አመልካቾች፡- 1. አቶ ተክሌ ዋቅጅራ
2. አቶ ጥላሁን ቦባስ
3. አቶ ሃቢብ መሐመድ
} ቀረቡ

መልስ ሰጭ፡- አቶ ሾንጣ ጉቡ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር አንድ አባል አገባለሁ ያለውን መዋጮ መቼና እንዴት ማግባት ያለበት መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

አመልካቾችና መልስ ሰጭዎች ጠቅላላ ግምቱ ብር 800,000 /ስምንት መቶ ሺህ ብር/ ካፒታል ያለው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሥርተዋል፡፡ የእያንዳንዳቸው መዋጮ ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ሲሆን የአሁን መልስ ሰጭ በዓይነትም ሆነ በገንዘብ አገባለሁ ካለው መዋጮ ውስጥ ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺ ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ብር/ ሣያስገባ ማህበሩ ሥራውን ሲያንቀሣቅስ ከቆየ በኋላ ሌሎች አባላት ይህንኑ ሊያስገባ የተስማማውን መዋጮ በገንዘብ ገቢ እንዲያደርግ ሲጠይቁት መልስ ሰጭ ይህንኑ መዋጮ ማህበሩ ከሚያስገኘው ትርፍ ገቢ በድርሻዬ



ከማገኘው እከፍላለሁ እንጂ እንደ ጥያቄያችሁ ክፍያውን ለመፈፀም ግዴታ አልገባሁም በማለቱ ምክንያት ይህ ክርክር ሊከሰት ችሏል፡፡

ይህንኑ ክርክር ያስነሣውን መዋጮ ገቢ ያደርግ ዘንድ አመልካቾች በጌዲኦ ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት ክስ መሥርተው መልስ ሰጭም ከላይ የተጠቀሰውን መከራከሪያ በማቅረቡ ይኸው ፍ/ቤት ጉዩን ተመልክቶ የአሁን መልስ ሰጭ ቀሪ አክሲዮን ድርሻውን /መዋጮውን/ በዚህ ጊዜ አስገባለሁ ብሎ ግዴታ አልገባም ማስጠንቀቂያ የደረሰው መሆኑም አልተረጋገጠም፣ ስለሆነም የሚከፍልበት ምክንያት የለም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁን አመልካቾች ቅር ተሰኝተው የይግባኝ አቤቱታቸውን ለደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅረባቸው ግራ ቀኙ በጉዳዩ ላይ ክርክር አድርገዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም የአሁን መልስ ሰጭ አስገባለሁ ካለው መዋጮ ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ብር/ ኣላስገባም (አልከፈለም) ሆኖም ይህንኑ ቀሪ ክፍያ ለመፈፀም ውል አድርጓል፡፡ ይህ ውልም ፈራሽ ነው አልተባለም ስለዚህ መልስ ሰጭ ገንዘቡን ሊከፍል ይገባል በማለት ዳኝነት ሰጥቶ ግራ ቀኙን አሰናብቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል የአሁን መልስ ሰጭ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቦ በሰበር ግራ ቀኙ ተከራክረዋል፡፡ ሰበር ሰሚው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ እንደሚከተለው ወስኗል፡፡

በንግድ ሕግ ቁጥር 338/1/ አክሲዮኖች በሚገዙበት ጊዜ እጅግ ቢያንስ ከተፃፈባቸው ዋጋ አንድ ሩብ ሊከፈል እንደሚገባ ወይም በሙሉ እንደሚከፈል ተደንግጓል፡፡ ዋጋቸው በሙሉ እስኪከፈል ድረስም አክስዮኖቹ በማህበሩ ስም የሚቆዩ ናቸው ሆኖም ይህ ያልተከፈለው አክሲዮን ማህበሩ በንግድ መዝገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ቢበዛ እስከ አምስት ዓመት ድረስ በየጊዜው መከፈል እንዳለበት በዚሁ ሕግ እና ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2

ተመልክቷል፡፡ በዚህ ሕጉ ባስቀመጠው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለው የአክሲዮን ክፍያ ካልተፈፀመ ምን ውጤት እንደሚያስከትል ደግሞ በንግድ ሕግ ቁጥር 342 ሥር ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ድርሻ የአክሲዮን ክፍያውን ገቢ አለማድረጉ ከተረጋገጠ በንግድ ሕግ ቁጥር 338/1/ እና 342 መሠረት

- ያልተከፈለባቸውን አክሲዮኖች ስም በማህበሩ ማቆየት፣
- በሐራጅ ማሸጥ፣
- ኪሣራ ካስከተለ መጠየቅ እንዲሁም ከጉባዔ ድምፅ እንዲታገድ ከሚድረግ

በቀር የአክሲዮን ክፍያ ገንዘብ አልከፈለም በሚል እንዲከፍል ማስገደድ ሕጋዊ መሠረት አይኖረውም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካቹ መክፈል የሚገባውን ቀሪ ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰላሣ ስምንት ብር ከሰማንያ ሣንቲም/ የአክሲዮን ክፍያ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ወስኖናል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ያመለክታሉ ያላቸውን ነጥቦች አመልካች በመጥቀስ እንዲታረምለት ነው፡፡

መልስ ሰጭም በበኩሉ የሥር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ግድፈት አልተፈፀመበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

እኛም ጉደዩን ተመልክተናል እንደተመለከትነውም አመልካቾችና መልስ ሰጭ ያቋቋሙት የንግድ ማህበር የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር ስለመሆኑና ክርክር ያስነሣውን የብር 74,838.80 መዋጮ መልስ ሰጭ ለዚሁ የንግድ ማህበር ገቢ ማድረግ በሚገባው ጊዜ ያላገባ ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የተካዱ ነጥቦች አይደሉም ፡፡ እያንዳንዱ ማህበርተኛ በዓይነትም ሆነ በገንዘብ ማግባት የሚገባውን መዋጮ አጠቃሎ መክፈል ያለበት መሆኑን ከንግድ ሕግ ቁ. 516 እና 517 ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡



ይኸውም ማህበሩ ተቋቁሟል የሚባለው በማህበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ ዓይነት በተዘጋጀው ግልጽ በሆነ ጽሁፍ ላይ ማህበርተኞቹ ወይም ወኪሎቻቸው የፈረሙበት እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ላይ ከሚገለፁት ነገሮች አንዱ የማህበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ መግባቱን የመጠቀሱ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲሁም በንግድ ሕግ ቁጥር 121 ሥር የአክሲዮኖች ድርሻ መዝገብ ምን ምን ነገሮችን ማካተት እንዳለበት ከተዘረዘሩት መካከል በንዑስ ቁጥር 1(ለ) "እያንዳንዱ ማህበርተኛ ማግባት ያለበትን የመዋጮዎች ግምት" የሚለው መዋጮው ከተቋቋመም በኋላ ወደ ፊት መግባት እንደሚችል በሚገልጽ አኳኋን የተፃፈ ቢሆንም **"the value of all contributions made by the members"** ከሚለው የእንግሊዝኛ ግልባጭ ጋር አጠቃለን ስናየው መዋጮ አስቀድሞ መግባት ያለበት መሆኑን የሚያመለከት ነው፡፡ እነዚህም ድንጋጌዎች ማህበርተኛው አገባዋለሁ ያለውን መዋጮ ማህበሩ በተቋቋመበት ጊዜ አጠቃሎ መክፈል ያለበት መሆኑን የሚያመለክቱ እንጂ ስለ አክሲዮን ማህበር በዚሁ ሕግ ቁ. 338/1/ እንደተመለከተው ክፍያ ሣይፈፀምበት ሊቆይ የሚችል መዋጮ ሊኖር የሚይችል መሆኑን አያሣዩም ማህበርተኞቹ ማህበሩን ሲያቋቁሙ በዚህ መሠረት መፈፀም ሲገባቸው አላደረጉም ሆኖም ማህበርተኛው መዋጮውን ዘግይቶ እንዲያስገባ በማድረግ ማህበሩን መሥርተው በተገኙ ጊዜ ማህበሩ ህልውና የለውም ማለት አይደለም፡፡ ይህንን አስመልክቶም የቀረበ ክርክር የለም፡፡ ይህ በጊዜው ገቢ ያልሆነው መዋጮ መቼ እና እንዴት መከፈል እንዳለበት በመመስረቻ ጽሑፍ ላይ ባይገለጽም መልስ ሰጭው ያልከፈለውና ገቢ ማድረግ ያለበት መዋጮ መኖሩን አምኖ እንደሚከፍል መተማመኛ የሰጠ ለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ የህንን መተማመኛ ከሰጠ በኋላ የአሁን መልስ ሰጭ የሚያቀርበው ክርክር ይህንን ገቢ ያላደረግሁትን መዋጮ ማህበሩ ከሚያገኘው ትርፍ በአስገባሁት መዋጮ ልክ ከሚደርሰኝ ገቢ እየተሰላ በየጊዜው ልከፍል ከሚገባ በቀር በአንድ ጊዜ የመክፈል ግዴታ የለብኝም የሚል ነው፡፡ ሆኖም ከላይ

እንደተመለተው የተወሰነ ኃላፊነት ያለው ማህበር መዋጮ መክፈል ያለበት ማህበሩ ሲቋቋም እንጂ ተቋቁሞ ሥራውን ከጀመረ በኂላ ባለመሆኑና መልስ ሰጭም ያላገባውን መዋጮ እከፍላለሁ በማለት እራሱን ግዴታ ውስጥ ያስገባ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ መተማመኛ የሰጠ በመሆኑ በሂደት ማህበሩ በሚያስገኘው ገቢ ልክፈል የሚለው መከራከሪያው ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት መዋጮ ሣይከፈል ከተገኘ በባለድርሻው ስም ሣይሆን በማህበሩ ስም ተመዝግቦ ሊቆይ እንደሚችልና መክፈል በሚገባው እጅግ ቢዘገይ በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለ ምን ውጤት እንደሚያስከትል በንግድ ሕግ ቁጥር 342 ተመልክቷል የሚለውን ምክንያት ይዞ መልስ ሰጭ ያላገባውን መዋጮ እንዲከፍል ማስገደድ አይቻልም በሚለው መደምደሚያው የጠ/ፍ/ቤቱን ውሣኔ ሊሽር የቻለው በንግድ ሕግ ቁጥር 338 እና 342 ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው ይሁን እንጂ እነዚህ ድንጋጌዎች የአክሲዮን ማህበርን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የአክስዮን ማህበርና የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር ሁለቱም የንግድ ማህበሮች ይሁኑ እንጂ በአመሠራረታቸው በአለባቸው የኃላፊነት አድማስ፣ በሚሰማሩበት የሥራ ዘርፍ ገደብ ያለባቸው ስለመሆኑና አለመሆኑ ወዘተ ስራ ልዩነት አላቸው፡፡ ለአክስዮን ማህበር የሚሸጡት አክሲዮኖች መቼ ገቢ እንደሚሆኑና ለተወሰነ ኃላፊነት ያለው ማህበር ደግሞ መዋጮው መቼ መግባት እንዳለበት በተለያዩ አኳኋን በየሚመለከታቸው ክፍሎች ተደንግገዋል መዋጮ መቼ መግባት ያለበት መሆኑን ስለአክሲዮን ማህበር የሚደነግጉትን ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ማድረግ እንደሚቻልም ተጠቅሶ አልተገኘም፡፡ ይህ ሆኖ እያለ የንግድ ሕግ ቁጥር 338 እና 342 አሁን ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት እንዳላቸው ቆጥሮ የክልሉ ሰበር ሰሚው ችሎት ለውሣኔው መሠረት ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡



**ው ሣ ኔ**

1. መልስ ሰጭ ለንግድ ማህበሩ ገቢ አደርጋለሁ ሲል መተማመኛ የሰጠበትን ብር 74,838.80 /ሰባ አራት ሺ ስምንት መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከ80%/ ገቢ ሊያደርግ ይገባል፤ ይከፈል ብለናል፡፡
2. የጌዲኦ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 22/92 በ24/3/95 የሰጠው ውሣኔ እና የደቡ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በይ/መ/ቁ. 5648 በ26/04/97 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
3. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 3694 በ29/4/96 የሰጠውን ውሣኔ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበተ

ተ.ወ